ምድብ	ቸርነት (10)	ዋኔን (11)
1	• አባታችን • አማን በአማን • ስለ ልደት	• አባታችን • በወንጌሉ • ስለ ልደት
2	• እግዚአብሔርም • ሰላም ለኪ	• እግዚአብሔርም • ሰላም ለኪ
3	• ስለቸርነትህ • በሕይወቴ • የእኛ ጌታ	• መጽኣ ቃል • ባርከን ባርከን • ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ
4	• ለእኔስ ልዩ ነች • ዮሐንስኒ ሃሎ	• የጥቡበ ሀገሯ • የድሆች መጠጊያ • ዮሐንስ
5	• ሰላምህ ይብዛላት • መች ይረሳል	• ሰላም ለማርያም • ድንቅ ነው • የዓለም መድኃኒት
6		• የጥቡበ ሰዎች • ስለድንግል ብሎ
7		• የአዋጅ ነጋሪ ቃል • የቅዱሳን በዓት

Contents

የጥምቀት መዝሙር - ቸርነት 2

1. አማን በአማን 2

2. ስለቸርነትህ 2

3. በሕይወቴ በዘመኔ 3

4. የእኛ ጌታ 3

5. ለእኔስ ልዩ ነች 3

6. ዮሐንሰኒ ሃሎ 4

7. ሰላምህ ይብዛላት 4

8. መች ይረሳል 5

የጥምቀት መዝሙር - ትዝታ 5

9. አባታችን 5

10. በወንጌሉ ያመናችሁ 5

11. ስለ ልደት 6

12. እግዚአብሔርም 6

13. ሰላም ለኪ 7

14. ወረደ ወልደ 7

15. መጽአ ቃል 7

16. ባርከን ባርከን 8

17. ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ 8

18. የጥቡበ ሀገሯ ወዴት ነው 9

19. የድሆች መጠጊያ 9

20. ዮሐንስ 9

21. ሰላም ለማርያም 10

22. ድንቅ ነው 10

23. የዓለም መድኃኒት 11

24. የጥበብ ሰዎች መጡ 11

25. ስለድንግል ብሎ 12

26. የአዋጅ ነጋሪ ቃል 12

27. የቅዱሳን በአት 12

አዲስ የተጨመሩ

1. ሀሌሀሌ ሉያ (ዘማሪ ኪነ ጥበብ)
2. ንሴብሖ ለአምላከ እዝራ
3. ሐዋርያት የሰበኩሽ
4. ይኸው ተወለደ
5. የበገና አካላት (የመጋቢ አለሙ አጋ ...በአዲቶሮያል ታይቶ)
6. ስለ ጥምቀት (የመጋቢ አለሙ አጋ... በአዲቶሮያል ታይቶ)

የጥምቀት መዝሙር - ቸርነት

1. አማን በአማን

(ሊ/መዘምራን ይልማ ኃይሉ) ቅኝት - ቸርነት

5-222-43-4-441542-2

1513 1445-5 15131-2-222

52-222-4-232423-3

445511-1-52-222-2

አማን በአማን /2/

አማኑኤል ተመስገን

ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ } 2x

ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልጠው

ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው

እንደ ሰው በቀል ቢኖርህ ጌታ

ለእኔ ኃጢአትስ የለውም ቦታ

አማኑኤል ተመስገን

ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ

በየደቂቃው ኃጢአት ስሠራ

ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ

አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም

በቁጣ በትር አልገረፍኸኝም

አማኑኤል ተመስገን

ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ

ምሕረትህን ልከህ አድነኝ ዛሬ

ታከቶኛልና በኃጢአት መኖሬ

ዓለም በኃጢአት እየሳበችኝ

በጽድቅህ ደስታ መኖር አቃተኝ

አማኑኤል ተመስገን

ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ

አማን በአማን /2/

አማኑኤል ተመስገን /2/

የኃጢአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም

ውጤቱ መርሮ ፍፁም አይጥምም

እንደ በደሌ ስላልከፈልኸኝ

ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

አማኑኤል ተመስገን

ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ

አማን በአማን /2/

አማኑኤል ተመስገን

ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ } 2x

2. ስለቸርነትህ

(ሊ/መዘምራን ይልማ ኃይሉ) ቅኝት - ቸርነት

231542-3 451342 2 (2x)

231542-3 231515 5 (4x)

ስለ ቸርነትህ ጌታ ተመስገን

ስለ ፍፁም ፍቅርህ አምላክ ተመስገን } 2x

ማነው የገመተ ከዛሬ መድረስን

ልብሱ ሳይነካ በእሳቱ ወላፈን

ባህሩን አሻግሮ ማዕበል አቁሞ

እርሱ ያውቅልናል ለመጪው ቀን ደግሞ

አዝ...

ሃሌ ሃሌ ሉያ መስዋዕት እናቅርብ

ጌታ ይፈልጋል የተሰበረ ልብ

ክርስቶስ ከሌለው ፍቅር ላይኖረው

ሰላም ሰላም ይላል ፍጥረታዊው ሰው

ሰላም ሰላም ይላል የዘመኑ ሰው

አዝ...

የጌታችን ነገር ለሚጠፉት ሁሉ

የመስቀሉ ነገር ለሚጠፉት ሁሉ

ሞኝነት መስሏቸው ከህይት ተሞሉ

የስንፍና አመል እያናወዛቸው

መጾም መጸለዩ ይጎዳናል ብለው

አምላክን ቢክዱ ፍቅርን ነፈጋቸው

3. በሕይወቴ በዘመኔ

(ሊ/መዘምራን ይልማ ኃይሉ ቁ.፩) ቅኝት - ቸርነት

23-42 2 14-15 5

15-11231-1 2223 42

2223 42 2 14-15-42 2

2223 42 2 2315-11231 1

በሕይወቴ በዘመኔ ደስ የሚለኝ ለእኔ በወንጌል
ማመኔ /2/

ሕይወቴ ቢመራ ጌታ በቃልህ
ብርታት አገኛለሁ ሲያድሰኝ ፍቅርህ
የአንተ ጸጋ ጌታ ስለበዛልኝ
ጨለማው ተገፎ ብርሃንህ መራኝ

አዝ... /2/

ወዴት እሄዳለሁ የእጅህ ጥበብ ሆኜ
ፍቅርህ እያደሰኝ ሞተህልኝ ድኜ
ምን ዓይነት መውደድ ነው አንተ ለእኔ ያለህ
ምን ይከፈልሀል ለፍጹሙ ፍቅርህ

አዝ... /2/

ምን ዓይነት መውደድ ነው አንተ ለእኔ ያለህ
ምን ይከፈለዋል ለፍጹሙ ፍቅርህ
ደጅህ ላይ ተጥዬ ደጅህ ላይ ልሙት
ቃልህን ልጠብቅ በፍፁም ፍርሃት

አዝ... /2/

4. የእኛ ጌታ

(ሊ/መዘምራን ይልማ ኃይሉ) ቅኝት - ቸርነት

231-42 2 231-42-2

23154 45-13 3
15131 43 42 2 } 2x

522224 23423 3 44551 52-22 2

15131 43-23 3 15131 43-42 2-(2x)

የእኛ ጌታ የእኛ መድኅን
በቸርነትህ ታደገን
እኛ እንደሆነ ኃይል የለን

አዝ...

ጠዋት ለምልማ ማታ ጠፋች
የሰው ህሊናን እያባባች
ዓለም ምኗ ነው የጣፈጠን
እያሳሳቀ የወሰደን

አዝ...

ዛሬ አለች ሲሏት ትጠፋለች
ከነተንኮሏ ዓለም ሟች ነች
እሾህ በቅሎባት እሾህ ሆና
በመተላለፍ ሰው ሊያልቅነው

አዝ...

ከእኛ ጋር ያለው ኃያል ነው
በሥጋዊ ዓይን ባናየው
የዶሩ ብዛት መች አድኗት
ዓለምን ትምከህት ተዋህዷት

አዝ...

እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኛ
እንደሰው ንብረት ወደረኛ
እንደ ዓለም ጉልበት ጉልበተኛ
በአምላክ ፊት ሲታይ ህመምተኛ

5. ለእኔስ ልዩ ነች

(ሊ/መዘምራን ይልማ ኃይሉ) ቅኝት - ቸርነት

233-42 2-42 423-15 13 31-31 (2x)

3-42 2-42 423-15 13 31-31 (2x)

233-42 2-42 423-15 13 31-31

233-42233 42 2-42 42

233-42 2-42 423-15 13 31-31 (3x)

233-42233 42 2-42 42

ለእኔስ ልዩ ነች ድንግል ማርያም
ለእኔስ ልዩ ነች እመብርሃን
ፈልጌ /4/ ላንቺ ምሥጋና አላገኘሁም /2/

ልቤ ሲያበቅል የኃጢአት አረም
ውስጤ ሲሸፍት አልተወችኝም
ከቤተ መቅደስ እጂን ዘርግታ
ትጠራኛለች የእኔ መከታ

የሆዴን ኃዘን የልቤን ምሥጢር
እነግርሻለሁ አንድም ሳይቀር
የምትሸሽጊ የሕዝብን ኃጢአት
ለእኔስ ልዩ ነሽ ድንግል አዛኝት

ጣዕሙ ልዩ ነው ከእርሷ ጋር መኖር
ድንግልን ይገፎ መቼም አላፍር
ወደ ጽድቅ ሕይወትትወስደኛለች
ድንግል ማርያም ለእኔ እናቴኮ ነች

በኃዘን ስሰበር ማንን እጠራለሁ
ውስጤ ሲደማ ለማን እነግራለሁ
ከኃጢአት እድፍ ንፁህ መሆኛዬ
አንቺ ነሽ ለእኔ የኔስ መጽናኛዬ

የኃጢአት ቁስል ያለአንቺ አይጠግም
ልጅሽ ሳይፈቅድ በሕይወት አልኖርም
ያላንቺ ምልጃ ለክብር አልበቃም
ከልጅሽ ሌላ መድኀን የለኝም

6. ዮሐንስኒ ሃሎ

(ዘማሪት ማርታ ኃ/ሥላሴ) ቅኝት - ቾርነት

43123-1 42-2-2324 22-2 3123-3 (2x)

መሸጋገሪያ 445 22-2

43122-2-2435-55-5

43122-2-2452 222-2

ዮሐንስኒ ሃሎ ያጠምቅ በሄኖን /፪/
ያጠምቅ በሄን
መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች እያለ
ዮሐንስ ሲያስተምር ማነው ያስተዋለ
እንደ ተናገረ አዋጅ ነጋሪው
ተራራው ዝቅ ይበል ይሙላ ጎድጓዳው
አዝ...
እድገቱ ምናኔ ትምህርቱ ንስሐ
የጣዝማ ማር በልቶ ኖረ በበረሃ
መጓዝ እንዲያስችለን በሕይወት ጎዳና
ላይ ታቹ ይደልደል ጎባጣውም ይቅና
አዝ...
ሲኖር በምናኔ በሄኖን በረሃ
ያጠምቅ ነበረ ዮሐንስ በውኃ
በማየ ዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ
ጌታ ተጠመቀ ድኅነትን ሊያውጅ
አዝ...
ጌታውን አጥምቆ ለክብር የሚበቃ
ከእናቱ ማኅፀን ተገኘ ምርጥ ዕቃ
ኤልሳቤጥም ለክብር ሆና የታደለች
መልካም የነፍስ አባት መጥምቁን ወለደች
ኤልሳቤጥም ለክብር ሆና የታደለች
መልካም የነፍስ አባት መጥምቁን ወለደች
ዮሐንስኒ ሃሎ ያጠምቅ በሄኖን/፪/ ያጠምቅ በሄን /፫/

7. ሰላምህ ይብዛላት

(ዘማሪ አቤል ተስፋዬ) ቅኝት - ቾርነት

መግቢያ 14513154245 5

14513154242 2

2315512422 4

2315512423 3

1451314222 2

4324551 2-311 1 1

4324551 42 222 4

231422 32423-3

14513142 222 2

ሰላምህ ይብዛላት ምድሪቱ
የሰው ልጅ እንዳይቀር በከንቱ /2/
አዝ...
የሌለንን ሰላም እንሰብካለን
በጎ ነገር ጠፍቶን እንጮሃለን
ጸሎት ልመናችን ከንቱ እንዳይቀር
ሰላምን ላክልን እግዚአብሔር
አዝ...
የካም ልጆች በዝተው በምድር ላይ
ገመናን ገለጡ በአደባባይ
ፍፁምነት ጠፍቶ ከልባቸው
በክፋት ተሞላ ጉባኤያቸው
አዝ...
በሰላም ቤት ቆመን ሰላም ጠፍቷል
ታንኳችን በንፋስ ተጨናንቋል
አድነን ጌታ ሆይ እንዳንጠፋ
ገስፀው ማዕበሉን ሁነን ተስፋ
አዝ...
ዓለም ስለ ሰላም ቢዘምርም
ምድራችን ከሰላም አርፋ አታውቅም

ሰላማችን አንተን ስንይዝ ነው
እውነተኛ ሰላም ምናገኘው
አዝ...

8. መች ይረሳል

(ዘማሪ አቤል ተስፋዬ) ቅኝት - ቸርነት

54224 23151551-1(2x)

15131 23151551 1

15131 23154 222 2

መሸጋገሪያ 52 52 4513 1551 1

52 52 4513 2332 42 2

መች ይረሳል የዋለልን ውለታ
ቸርነቱ እፀብ ፍቅሩ የጌታ
የታተመው በልባችን ጽላት
ሞትን ገድሎ የሠጠንን ሕይወት
በጥፋቱ ቢወጣ አዳም ከገነት
ቃል ገባለት ዳግም ሊሠጠው ሕይወት
ህያው ጌታ አምላክ ፈጣሪ ሳለ
ስለ ቃሉ በእፀ መስቀል ላይ ዋለ
በአይሁድ እጅ በጽኑዕ ተንገላታ
የፍቅር አባት ክርስቶስ የእኛ ጌታ
ሥጋው ደክሞ ቅዱስ ደሙ ፈሰሰ
እዳችንን በሞቱ ደመሠሠ
ስንጠላው እርሱ አብዝቶ ወደደን
ስለ ፍቅሩ ሞትን ገድሎ አዳነን
ባርነትን ኃጢአትን ከኛ ጥሎ
ነፃ አወጣን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ
ሰላማችን የድንግል ማርያም ፍሬ
ይገባዋል ምስጋናና ዝማሬ
ስለ ፍቅሩ ስላረገልን ሁሉ
ተቀኙለት ፍጥረታት ዝም አትበሉ

የጥምቀት መዝሙር - ትዝታ

9. አባታችን

(መ/ስብሐት አለሙ ኢጋ) ቅኝት - ሰላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222

አባታችን በሰማያት ላይ ያለህ
ተለይቶ ይመስገን ቅዱስ ስምህ
መንግሥትህን የምንፈልጋት ከጥንቱ
በልጅነት ትምጣ ትሰጠን አቤቱ
ፈቃድህም ይህ እንዲደረግ ይሁን
በሰማይም ሞተን ተነስተን ከደይን
እንድንኖር ምስጋናህ ምግብ ሆኖን
ዛሬም በምድር በሥጋ ሕይወት ሳለን
ምግባችንን በየለቱ አውቀህ ስጠን
ይቅር በለን የበደልንህን ነገር
ወንድማችን የበደለንም ቢኖር
እንዳቅማችን እኛም እንድንል ይቅር
ከገሃነም ከክፉ ሁሉ መአት
አትጣለን አድነን እንጂ ከሞት
ይህቺን መንግሥት የማያገኛት ህልፈት
ጌትነትም ከሀሊነትም ክብርም
ናቸውና የአንተ ገንዘቦች ሁሉም
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን::
የተላከው ቅዱስ ገብርኤል ከጌታ
ሰላም ለኪ ብሎ በሰጠሽ ሰላምታ
እኔ ባሪያሽ ልብሴን ስታጠቅ ስፈታ
ሰላም ልልሽ ይገባኛል ጠዋት ማታ
ማርያም ሆይ እመቤቴ ሆይ ድንግል
በሥጋሽም በህሊናሽም ድንግል
የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ድንግል
እንዳለሽ ቅዱስ ገብርኤል ሰላም
ሰላም ለኪ እንደርሱ ሁሉ እኔም
የሌለብሽ የነፍስ የሥጋ መርገም
ቡሩክ ነው የማህፀንሽ ፍሬም
እንደቀድሞው ቡሩክ አምላክ ነው ዛሬም
እግዚአብሔር ወልድ በመጣ ጊዜ ለካሳ
እንበለ ዘር እንደ ጉብ እና እንደ ዓሣ
ከነፍስሽ ነፍስ ከሥጋሽ ሥጋ ቢነሳ
ደስ ያለሽ ሆይ ጸጋን አግኝተሽ ከጌታ
ደስ ይበልሽ በማቀርብልሽ ሰላምታ
ለምኚልን ሳትሰለቺ ጠዋት ማታ
ውድ ልጅሽ እንዲያደርግልን ይቅርታ
ይቅር ብሎ ኃጢያታችንን ሁሉን
እንዲያድነን በአንቺ ተማፅነን አለን
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን::

10. በወንጌሉ ያመናችሁ

(ቅኝት - ትዝታ)

1332422-2-2-2-2 (2x)

52-2 423-3 123-4 2-2-423-3

52-2 423-3 123-4 2-2-222-2

በወንጌሉ ያመናችሁ /2/

11. ሰለ ልደት

(መ/ስብሐት አለሙ ኢጋ) ቅኝት - ሰላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222 2

ድንግልም በምትወልድበት ወራት
በሮም ንጉሥ በአውግስቶጦስ ቄሳር መንግሥት
ሰው ሁሉ ግብር ሊቆጠር ታዘዘ
ዮሴፍም ድንግልን ይዞ ተጓዘ
ከገሊላ ከነበረበት መንደር
ቤተልሔም ወደምትባል ሀገር
ከኤፍራታ ይወጣል ብሎ ንጉሥ
ሚከያስ የተናገረው ሊደርስ
ሳታፋልስ የወላዶችን ሥርዓት
በታኅሣሥ ሃያ ዘጠኝ ዕለት
ከዚያው ሳሉ የምትወልድበት ቢደርስ
ተወለደ ድንግልናዋን ሳይጥስ
ቤት ባይኖራት መጥታለችና ከሩቅ
ከበረት ጠቀለለችው በጨርቅ
ሊፈጸም የኢሳይያስ ነገሩ
እንስሳትም ትንፋሻቸውን ገበሩ
ከዚያ ቦታ ከብት ጠባቂዎች ነበሩ
ያዩ ነበር ካሉበት ቦታ ድረስ
የብርሃን ጎርፍ ከቤተልሔም ሲፈስ
እረኞቹም የብርሃኑን ጎርፍ አይተው
እጅግ ፈሩ ምን ነገር ነው ብለው
መልአኩም ፍርሐታቸውን አርቆ
ነገራቸው ተድላ ደስታውን አድንቆ
ልዑል አምላክ ለአዳም ብሎ ተዋርዶ
ከድንግል በዳዊት ባሕርይ ተወልዶ
ጨርቅ ለብሶ ከበረት መሐል ተጥሎ
አለላችሁ ሄዳችሁ እዩት በቶሎ
እንዲህ ብሎ ሲናገራቸው በዜና
ከእርሱ ጋራ ብዙ መላእክት መጡና
አቀረቡ ከእረኞች ጋር ምስጋና
ስብሐት ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

12. እግዚአብሔርም

(መ/ስብሐት አለሙ ኢጋ) ቅኝት - ሰላምታ

4245 313 15423 312 45

4245 313 15442 222 2

እግዚአብሔርም አዳም ባጠፋው ጥፋት
በተስፋ ቃል አሰናበተው ያን ዕለት
ለአዳም በገባለት ቃል ኪዳን
አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን
ሲፈፀም ያ የተስፋ ቃል ደረሰ
የአዳም የስቃይ ዘመን ፈረሰ
አዳምም ሲኖር በሲኦል ተቀብሮ
አዳነው ሞቱን በሞቱ ቀይሮ
አምላክም ወደዚህ ዓለም ሲመጣ
ቆየችው እመቤታችን ተመርጣ
የሌለባት መርገም ፍዳ ከጥንት
ጸነሰችው በመልአኩ ቃል ብሥራት
ፍቅር ስቦት ወደዚህ ዓለም መጣና
ለአዳም ምን ያልሆነለት አለና
ተወለደና ድንግልናዋን ሳይሸር
ለሰው ልጅ ሲል ተመላለሰ በምድር
በዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ
በዲያብሎስ የተጻፈውን ተራምዶ
አጠፋለት ያንን ደብዳቤ ደምስሶ
ከባርነት የሚያላቅቀው ጨርሶ
በመስቀል ላይ በዕለተ ዓርብ ተወግቶ
ከሲኦል በደሙ አነፃው አውጥቶ
እንዲህ አድርጎ ወደ ጥንት ቦታው መለሰው
በምህረቱ ዳግም ገነትን አሳየው
በአባታችን በአዳም ጥፋት በደል

ገብተን ነበር እኛ ሁላችን ሲኦል
በሥራችን በኃጢአታችን እኛማ
ሆነን ነበር ከመርገም ግዞት ጨለማ
ግን አዳነን የፍቅር አምላክ ነውና
በትህትና እናቀርብለት ምስጋና
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

13. ሰላም ለኪ

(መ / ስብሐት አለሙ ኢጋ) **ቅኝት - ሠላምታ**

4245 15423 312 45

4245 15452 222

ሰላም ለኪ ማርያም ደንግል ንጽሕት /3/
ያቺን ርግብ ያቺን ወለላ ፍጥረት
በበገና እስኪ ላመስግናት ጥቂት
የአምላክ እናት የሰማይ የምድር ፈጣሪ
የእርሷ አዝማሪ ዕዝራና ዳዊት በባህሪ
ቃል ኪዳኗ የማይፈርስባት ነዋሪ
እልፍ አዕላፍ መላእክት አሉዋት ነባሪ
ያገልግሉሽ ብሎ የሰጣት ፈጣሪ
እኒያን ይዛ ፍጥረት ዓለሙን መካሪ
ወለላዊት ቤዛዊት ዓለም ብፅዕት
ከወተት ውዳሴሽ ጥዑም በእውነት
ከወለላ ተአምርሽ ጥዑም ሲበላ
የብርሃን ዘውድ የብርሃን አክሊል ደፍተሽ
ድረሺልን በሠረገላ ሁነሽ
ይሸሻሉ አጋንንት አንቺን ሲያዩሽ
በቤተ መቅደስ ስታገለግል ስትሠራ
ነይ ውጭ አሏት ሊቃውንት መከረው በሴራ
ተመቅኝተው ምናምን ኃጢአት ሳትሠራ
እንደ ፀሐይ ገለዋ እንደ እሳት ሲያበራ
ትሙት ብለው ማየ ዘለፋን ቢያጠጧት
እንደገና ብርሃን መሆኗ ባሰባት
ያንን ግሩም ያንን ደስ የሚል መዐዛ
በንጽሕና ያለሩካቤ /ፀንሳ/ አርግዛ
ወለደችው በቤተልሔም ተጉዛ
ምጥ የለባት በመላአክ እጅ ተይዛ
የታደለች የተባረከች ፍጥረት
የበላውን ሰባ ስምንቱን ነፍሳት
አስገባችው በጥርኝ ውሃ ገነት
ከአድማስ አድማስ ወረቀት ቢሆን መሬት
ቀለም ቢሆን የሦስት ወር ውሃ ከረምት
ብዕር ቢሆን የዚህ ዓለም ሁሉ ዕፅዋት
ቢጻፍ አያልቅም የተአምርሽ ብዛት
ንግበር ብሎ ገና ሲፈጥረን ከጥንት
ፈጥሮ ሰጠን ድንግል ሕሊና ትሁት
በእርሷ ሰበብ እንባለን ገነት
ተመልከቱ የእግዚአብሔርን ምሕረት
ብንወርድበት መቼ ይወዳል ከእሳት
እኛ ግና በኃጢአታችን ብዛት
እንወድቃለን ከዚያ ጨለማ ክርፋት
አደራሽን በዛዊት ዓለም ብፅዕት
በማልቀስሽ በመጨነቅሽ ብዛት
ሑሩ ሲለን እንድታወጪን ከእሳት
ቃል ኪዳንሽ እጅግ ታላቅ ነው ከጥንት
አንቺን አምኖ እንዴት ይጎዳል ፍጥረት
ማጎደሩ የአምላክ ሰማይ እናት
ታይቶ አይጠገብ ሁልጊዜ የልጅሽ ምሕረት
እኛን በቀኝ እንድታቆሚን ያን ዕለት
ስብሐት ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለአለም ድረስ።።

14. ወረደ ወልድ

ቅኝት - ትዝታ

52 222 4 23 555-1 54 555-5

3524513 542 545 5

3524513 542 222-2

35-5 ኧኸ

ወረደ ወልድ /3/
እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት /2/ ኧኸ
ትርጉም፡- ወልድ ከርስቶስ
ከሰማያት ወደ ወንዞች ወረደ

15. መጽአ ቃል

ቅኝት - ትዝታ

2-222-2 31 54 4452 5515

2-1-113 1 2245 21-113-3

2-1-113 1 2245 42 222-2 31-1 (2x)

መፃ ቃል እም ደመና ዘይብል /2/ /2/

ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር /4/ ኧሽ

መጣ ቃል ከደመና እንዲህ የሚል /2/

የምወደው የማፈቅረው ልጄ ይህ ነው /4/

16. ባርከን ባርከን

2-2224-2314-333-3 (2x)

21-13-113-1 223 113 3

21-13-113-1 432 222 2

31-1 (ኧሽ)

21-13-113-1 223 113 3

21-13-113-1 432 222 2

ባርከን /2/ ልጆችህን ባርከን /2

በቅዱስ መንፈስህ አንድ ሐሳብ አድርገን **ኧሽ**/2/

ባርኪን /2/ ልጆችሽን ባርኪን /2/

ድንግል ሆይ በምልጃሽ አንድ ሐሳብ አድርጊን

ድንግል ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አስታርቂን **ኧሽ** 2x

ጥሪህን ስንሰማ ወዳንተ እንድንመጣ

በሕግህ ልንኖር ከቤትህ ሳንወጣ

በሕይወት ስንደክም እንዳንጠፋ በዓለም

እርዳን ፈጣሪያችን ቸሩ መድኃኔዓለም

ባርከን /2/ ልጆችህን ባርከን /2

በቅዱስ መንፈስህ አንድ ሐሳብ አድርገን /2/

ከተፈረደብን የባርነት ሕይወት

ከመጣብን መርገም በመብል ምክንያት

ከሲኦል እሥራት እኛ የዳንብሽ

ድንግል ሆይ ምን ጊዜም አይለየን ምልጃሽ

ባርኪን /2/ ልጆችሽን ባርኪን /2/

ድንግል ሆይ በምልጃሽ አንድ ሐሳብ አድርጊን

ድንግል ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አስታርቂን

አንድነት ስናጣ ፍቅር ስትመነምን

በምግባር ስንደክም ሲጐድል እምነታችን

በሥጋችን ፈቃድ ወድቀን እንዳንጠፋ

በምሕረትህ ጐብኘን አንተ ሁነን ተስፋ

ባርከን /2/ ልጆችህን ባርከን /2

በቅዱስ መንፈስህ አንድ ሐሳብ አድርገን /2/

ርኅርኅተ ኅሊና ቅድስት እናታችን

አሳስቢ ሁልጊዜ ስለኃጢያታችን

ሊያድነን ነውና ክርስቶስ መሞቱ

አስምሪን እመአምላክ ድንግል ወላዲቱ

ባርኪን /2/ ልጆችሽን ባርኪን /2/

ድንግል ሆይ በምልጃሽ አንድ ሐሳብ አድርጊን

ድንግል ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አስታርቂን **ኧሽ** 2x

17. ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ

(ሊ/መዘምራን ይልማ ኃይሉ) ቅኝት - ትዝታ

213 24552 42 421 11553 23

213 24552 42 342 22-2 42

213 24552 42 421 11553 23

213 24552 42 342 222 42 /2/

15-113-42 42 421 11553 23

15-113-42 42 452 22-2 42

ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ ክብርንም ልበሺ

በአዲስ ምስጋና ይመላ ልብሽ

የተወደደ ነው በእግዚአብሔር ህዝብሽ/2/

ንብረቱ ጠፊ ነው ከንቱ የማይረባ

በግፍና ቅሚያ በአመፅ ሲገነባ

ሲሳይሽ ብዙ ነው ከአምላክ የተሰጠሽ

በረከት ለማግኘት መሥራት ነው ጠንክረሽ

የአህዛብ ብልጽግና አያስቀናሽ ፍፁም

ኃላፊ ጠፊ ነው ምኞቱም ዓለሙም

ደመና ነውና ይበናል በቅጽበት

በግፍ የተገኘ የተከማቸ ሀብት

ይልቅ በቅንነት በሰላም ለሰራ

ሲሳዩ ብዙ ነው ክብሩም አያባራ

ጉቦና ፍትህን ማጣመም እንዳንለምድ

ከወንጌሉ ጋራ አለብን መዛመድ

እግዚአብሔር ያለው ሰው በእርሱ የታመነ

ከግፍ ሥራ ሕመም አካላቱ ዳነ

ክርስቲያን ነኝ ብሎ ጉቦ የሚበላ

የሚቃጥል እሳት ያገኘዋል ኋላ

በመታመን ጸጋ ይጠራ ስማችን

እውነተኛ እንሁን ለውድ ሀገራችን

የራሱን ሳይሻ ለሀገር የሚያስብ ሰው
በእግዚአብሔር ዘንድም የተወደደ ነው

18. የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው

(ሊ/መዘምራን ኪነጥበብ ወ/ቂርቆስ) ቅኝት - ትዝታ

211 55-2-2 21 13 24-4

211 55 23 32 2

135-5 3132-2 135-5 3111-1

135-5 3132-4-42 2222-2

መሸጋገሪያ 135-5 3132-4-42 2222-2

የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው
ማደሪያዋስ ወዴት ነው } 2x

አዝ...
ቦታ ጎዳናዋ ከወዴት ተቃኘ
ዝናና ወሬዋ ከወዴት ተገኘ
ፈልጎ የገዛት ማነው በቀይ ወርቅ
ባሕሩን ተሻግሮ ስሟን በማወቅ
አዝ....
ማን ነው ያወረዳት ከደመና በላይ
ድምጿንስ የሰማ ከላይ ከሰማይ
እሷን የሚጠሉ ናቸውና ከንቱ
አይቀርላቸውም ኋላ የሞት ሞቱ
አዝ...
ሁሉን የሚያውቅ እርሱ እርሱ ያውቅላታል
ቦታ ጎዳናዋን ያሳምርላታል
በክርስቶስ ፈቃድ በምድር ላይ ታየች
እነሆ ቤት ሠራች ሰባት ዓምድ አቆመች
አዝ...
ጥበብ ግን እርሱ ነው መድኃኒታችን
በሥጋ ተገልጦ እኛን ያዳነን
በደሙ ፈውሶ የተወዳጀን
ለእርሱ የመረጠን ይክበር ይመስገን /2/

19. የድሆች መጠጊያ

/ዘማሪት አዳነች አስፋው ቁ.1/ ቅኝት - ትዝታ

2-423-24-5 5-154-32-2 (2x)

21-13513-1-24-4 2151 1

2 1-13513-1-24-2 542-222-2

2-4 235-5 1-113113 1-113113 3

2-4 23-124 2 542 222

የድሆች መጠጊያ ቤተክርስቲያን /፪/
እነሆ ተደሰች ልጆችሽ መጣን /፪/
ሰላም ሰላም <u>የዘለዓለም ቤቱ</u> /፪/
ከአንቺ ፈልለይም እስከ ዕለተ ሞቱ } *2x*
ሰላም ላንቺ ይሁን ቤተ ክርስቲያን /፪/
በደሙ ያፀናሽ ኢየሱስ መድኅን /፪/
አዝ...
ቤተ ክርስቲያን ሆይ የአማንያን እናት /፪/
ወደ አንቺ ቀርበናል እንድናገኝ ሕይወት /፪/
አዝ...
ቅረቡ ምእመናን በአንድነት ሆናችሁ /፪/
እጆቿን ዘርግታ ልትቀበላችሁ
ተነሥታለችና ቅድስት እናታችሁ
አዝ...

20. ዮሐንስ

(ዘማሪት ማርታ ኃ/ሥላሴ) ቅኝት - ትዝታ

11131 4225-4 322222 <u>2</u>

211-1131 422 225-<u>5</u>

211-1131 422 222 <u>2</u>

ዮሐንስ/2/ ሔደ ዮርዳኖስ/2/
የበደለውን ሕዝብ ጠርቶ ለንስሐ
ያስተምር ጀመረ ገብቶ በበረሃ
አባጣ ጎባጣ ጠማማው ኮረብታ
ይስተካከል አለ ሁሉም በየቦታ (2)
አዝ...
በዮርዳኖስ ማዶ በሄኖን ከተማ
የንስሐ ጥሪ በሩቁ ተሰማ
ግመል ጸጉር ለብሶ ወገቡን ታጠቀ
ዮሐንስ ተመርጦ ጌታን አጠመቀ /2/
አዝ...
ባሕር ተጨነቀች ሸሸችም በፍርሃት
እሳተ መለኮት እንዳያቃጥላት

መንፈስ ቅዱስ መጣ ሊሆነው ምስክር
ከአብ መወለዱን ልጅነቱን ሊያከብር /2/
አዝ... /4/

21. ሰላም ለማርያም

(ዘማሪት ሶስና) ቅኝት - ሰላምታ

54 2333 2333 22 42245

54 2342 224 515 13

1542 2242 224 515

ሰላም ለማርያም የአምላክ እናት
የአቤል የዋሃት የአዳም ሕይወት
እመቤቴ በምልጃሽ መድኃኒቴ ነሽ
የአብ ቃል መቅረጫ ጽላቱ የሙሴ
የመንፈስ ቅዱስ ቤት እመቃል ሞገሴ
የርኅራኄ መዝገብ እህተ መላእክት
የጻድቃን ተስፋቸው ጽላተ መለኮት
ትናንት ተጨነቅን በጨለማው ዓለም
ዛሬ ብርሃን አየን በድንግል ማርያም
የኢያቄም እንቁ የሃና ንብረቷ
ሥጋ ነፍሴን እርጂያት ይቅርላት ቅጣቷ
በወንጌል ሰማነው ድንግል የአንቺን ዜና
አማላጅነትሽ ሲገለጽ በቃና
ከዳዊትም ሰማን ድንግል ስለአንቺ ክብር
ወትቀውም ንግሥት እያለ ሲዘምር
በላዔ ሰብዕ ከሞት ከሲኦል የዳነው
በምልጃሽ ነው እንጂ መች በጥርኝ ውኃ ነው
ሊውጡኝ ቢነሱ ኢጋንንት በሙሉ
ስምሽን ስጠራ ትቢያ ይሆናሉ
ጽዮን እመብርሃን ጽላተ ሥላሴ
የበረከት ካዝና ደመወዜና ዋሴ
ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ ሲከፋኝ ኑሮዬ
ድንግል አንቺ እኮ ነሽ አጽናኝ አለኝታዬ
ስምሽን ስጠራ ሲታወክ ህይወቴ
አለሁልሽ በይኝ ድንግል እመቤቴ
ድንግል ሆይ አትርሺኝ የዘላለም ልብሴ
ምልጃሽ ያውጣኝ ከሞት ከከፋ ድምሳሴ
የቅዱሳን ካባ የቅዱሳን ኩታ
ጸጋ ሰማዕታት የድሆች አለኝታ
ሹመተ መሳፍንት ቅብዐ ነገሥታት
የሰለሞን እውቀት የዳዊት መዝሙራት
ዓለም የዳነብሽ ከሞት ከሲኦል
ለእኔስ እናቴ ነሽ ማርያም ድንግል
ኡድኚኝ እናቴ ከሥጋ ፈተና
እኔማ ያለአንቺ አልችልም ልጸና
ሸክም የከበደኝ እንግልት ሆኖለሁ
ከእኔ እንዳትለይ አደራ እልሻለሁ
አደራ እልሻለሁ ከጎኔ አትራቂ
ወዳጅ ዘመድ የለኝ ያለአንቺ ጠባቂ
ተሳከቶልኝ ባየው ሀሳቤ ምኞቴ
ድንግል ያላንቺማ መች ይፀናል ቤቴ
ልጅሽ እንዳይነሳኝ መንግሥተ ሰማያት
ከኃጢአት ጠብቆ እንዲያኖረኝ ገነት
አንቺ ንገሪልኝ ለዓለም መድኃኒት
ተስፋዬ ነሽና አትርሺኝ የኔ እናት
እመቤቴ በምልጃሽ መድኃኒቴ ነሽ /2/

22. ድንቅ ነው

/ማኅበረ ቅዱሳን ቁ. ፮/ ቅኝት - ትዝታ

545 3123 145-1 545145 5

545 3123 3224 234 222 2

545 211 132 213 3

545 213 331 432 2

ድንቅ ነው ልዩ ነው ልዑል የእኛ ጌታ
ምስጋና ይድረስው ከጠዋት እስከ ማታ /፪/
አዝ...
የማይመረመር በሰው ልጅ ኅሊና
ረቂቅ ባሕርይ ገናና ነውና
ያለ የነበረ ከዘመናት በፊት
ለዘላለም ኗሪ ፈጣሬ ዓለማት
አዝ...
በፍጥረታት ሁሉ የሚመሰገነው
ኃያሉ ጌታችን በእውነት ልዩ ነው
በፍጹም ልዩ ነው የእርሱ ጌትነቱ
አልፋና ዖሜጋ ጽኑዕ ነው መንግሥቱ
አዝ...

በመላእክት ዓለም በሰማይ ከተማ
ለክብሩ ሲዘመር ማኅሌት ሲሰማ
ያለምንም እረፍት በቀንና ሌሊት
ንጹሐን መላእክት የሚያመሰግኑት
አዝ...
አዳምን ለማዳን ፍጹም በመውደዱ
የማይሞተው አምላክ ሞተ በፍቃዱ
ምሥጢሩ ረቂቅ ነው ለሰዎች አእምሮ
በፍቅሩ ያስደንቃል ስናየው በእንክሮ

23. የዓለም መድኃኒት

525231 1 2324 22245 5
525231 1 211111 1
525231 1 211111 1 (*መሸጋገሪያ*)
113 3 15 332 2 324-421-113 3
444 542 2 1113231 1
444 542 4 234222 2
የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተልሔም የተቀደስሽ ነሽ
የአማልክት አምላክ ንጉሠ ነገሥት
ኃያላን በሙሉ የሚሰግዱለት
በጨርቅ ተጠቅልሎ ተኛ በበረት
አዝ...
የጥበብ ሰዎች በቅን ሀሳባቸው
ወደ አንቺ ተጓዙ ኮከብ ሲመራቸው /2/
አዝ...
ለተከታይ ትውልድ ምሳሌ ለመሆን
ሰግደው ገበሩለት ወርቅ ዕጣን ከርቤን/2/
አዝ...
የሚያድለው ጌታ እውቀት ለሕጻናት
የሚመሰገነው በአፈ መላእክት
ከእንስሳት ጋራ አደረ በበረት
አዝ...
ሥጋ ለብሶ ቢታይ ረቂቅ መለኮት
በአንድ ላይ ዘመሩ ሰውና መላእክት /2/

24. የጥበብ ሰዎች መጡ

5242322 2 52415455 5
523112 432 222 2
11123 545 5 54512313 3
313231 1 2324234 232432 2
***መሸጋገሪያ* 2324234 232432 2**
ሰማይና ምድር የማይወስኑት
ተወስኖ አየነው በጠባብ ደረት
ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ
አገኘነው ዛሬ በበረት ተኝቶ
የጥበብ ሰዎች መጡ/2/ ሰምተውት በዜና
እያበራላቸው ኮከብ እንደ ፋና/2/
ድንግል እመቤቴ ሰላምታ ይድረስሽ
ለአምላክ ወገኖች መመኪያቸው የሆንሽ
ካንቺ ተወለደ የዓለም መድኅን
ኩነኔን አጥፍቶ ጽድቅን ሊያወርስን
አዝ...
ጌታችን ሲወለድ በቤተልሔም
ሐዘን ተደምስሶ ሰፈነ ሰላም
እንጨቶች አፈሩ ፍሬ በረከት
ወንዞች ሁሉ ሆኑ ማርና ወተት
አዝ...
ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ
የእሥራኤል ንጉሥ ወዴት አለ እያሉ
እጅ መንሻውን ሰጡት እንደየሥርዓቱ
ዕጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግሥቱ
ከርቤውን ለሞቱ
አዝ..

25. ስለድንግል ብሎ

52 23 24 5-3 52-4 23-42 22 2(2x)

35-54 51 3-2-4 23-5 54 45 5 5

35-54 51 3-2-4 23 42 22 2(2x)

ስለድንግል ብሎ ኢትዮጵያን ይጎብኛት
ድሮስ ከአምላክ በቀር ይች አገር ማን አላት
በሥራዊት ብዛት መች ትጠበቃለች
በቅዱሳን ጸሎት እሳት ካልታጠረች /2/
አዝ...
ዓለም ሸምቆባት አሕዛብ ይስቃል
በልጆቿሽ እንባ አውሬው ይቀልዳል
ታላቅ ሕዝብ መሆኑን ማንበነገራቸው
ከዘመናት በፊት አምላክ የነበኘው /2/
አዝ...
እውነተኛው እንባ ፈለቀ ከምድር
በፍጡራን ዋይታ ፍጹም ብትማረር
እንባና ደማችን ተደባልቆ ፈሷል
አምላክ ቅጣት ይብቃን አሁን ይቅር በለን /2/
አዝ..
ቅዱሳንን መንቀፍ ወገኔ ተውና
ይልቅ ስለ እነሱ የጽድቅ ጎዳና
በረድኤታቸው በክብራቸው ጥላ
እንከተላቸው ከፍቅራቸው ኃላ

26. የአዋጅ ነጋሪ ቃል

35551531-1 52245 155 5
522-45113-3 51513242-2 (2x)

3555115131313154-425-5
52-231-153-3245232-2 (2x)

የአዋጅ ነጋሪ ቃል በበረሃ አየለ
የእግዚአብሔርን መንገድ አስተካክሉ እያለ
ምስክርነቱን ዮሐንስ ካስረዳን
ልባችን ለጌታ መልካም መንገድ ይሁን

የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም
አውደ ዓመቱን ባርኪልን ድንግል ማርያም2x

ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና
ካልተስተካከለ መንገድ የለምና
የእግዚአብሔርን መንገድ እንመሥርት ሁላችን
ማለፊያ እንዲሆነን ለመጭው ሀብታችን
አዝ...
ክፋትና ተንኮል ከልባችን ይጥፋ
ጽድቅና ርኅራሄ በእኛ ላይ ይስፋፋ
ሥጋና ደምህን በክብር አግኝተናል
ሕይወት እንዲሆነን አምላክ ተማጽነናል
አዝ...
ሁለት ልብሶች ያሉት ከማብዛት ልብስን
ለሌለው ያድለው ሁለተኛውን
ከበደላችንም አንፃን አደራህን
በከፉ እንዳንጠፋ እኛ ባሮችህን
አዝ...

27. የቅዱሳን በኣት

352-2242 352-224 154
352-2242 145-555 315
3123 1554 2324 23-3
3123 1554 2324 15 5
3123 1554 2324 15 5 (መሸጋገሪያ)

ልቡና የሚመስጥ መዓዛ ዕጣኗ
ጎሊናን ይገዛል ዝማሬ ድጓዋ
የቅዱሳን በዓት የጸሎት ዋሻቸው
ቤተ ክርስቲያን ናት አምባ መጠጊያቸው
የመላእክት ዜማ የአእዋፍ ዝማሬ
የሚለቀምባት የትሩፋት ፍሬ
ይዘምሩባታል በአንድነት ተባብረው
የሌዋዊው በትር ጸናጽል ከበሮው
ወራዳዋን ዓለም የናቋት በቅድሚያ
የእምነት አርበኞች ያነፂት በፍልሚያ
የገድላቸው ተዓምር መንበግቦኒያ መቅረዝ
የሰማዕታት አክሊል የሥራቸው ደመወዝ
መውደቂያዬ ይሁን ከመቃብራቸው
ይፈውሳልና ተረፈ አጽማቸው
ከኃጥአን ድንኳን መውጣቴ ነው ዛሬ
የቅዱሳን በኣት ልትሆነኝ አገሬ
የቅዱሳን በዓት የጸሎት ዋሻቸው
ቤተ ክርስቲያን ናት አምባ መጠጊያቸው 2x

አዲስ የተጨመሩ መዝሙሮች